የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር
FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
MINISTRY OF FORIEGN AFFAIRS

ቀን Date. የካቲት 12 2016

ቁጥር No. ፓ.ፕ.ጋ/352/16

ለኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ኤምባሲዎች፣ ቋሚ መልዕክተኛ ጽ/ቤቶች እና ቆንስላ ጽ/ቤቶች

<u>በያሉበት</u>

ኢትዮጵያውያን በተለያዩ የአለማችን አገራት ዩኒቨርስቲዎች የትምህርት እድል አግኝተው ለሚሄዱ ተማሪዎች ትምህርታቸው አጠናቅቀው ወደ አገር ቤት ከመመለሳቸው በፊት ትምህርቱ በተከታተሉበት አገር በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ወይንም በሚመለከተው የመንግስት ተቋም ትምህርታቸውን በአግባቡ ስለማጠናቀቃቸው የተሰጣቸውን ማስረጃ ካረጋገጡ በኋላ በዚያው አገር በሚገኘው (ሀገሪቱን በሚሸፍነው) ኢፌ.ዲ.ሪ. ኤምባሲ ወይንም ቆንስላ ጽ/ቤት ዶክመንታቸው ተረጋግጦ ወደ ሀገር ሲገባ፡ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የቆንስላ ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ጀኔራል ዶክመንቶቹን መረጋገጥ ይጠበቅበታል። የከፍተኛ ትምህርት አግባብነትና ጥራት ቁጥጥር ባለስልጣንም በተለያዩ አገራት ትምህርታቸውን በተሳካ ሁኔታ አጠናቅቀው ለሚመለሱ ተማሪዎች የተሰጣቸውን ዶክመንት በኢ.ፌ.ድ.ሪ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር መረጋገጡን በማየት የአቻ ግመታ ይሰጣል። ይህ ካልሆን ከውጭ አገር የሚገባ የትምህርት ማስረጃ አገር ውስጥ አገልግሎት ላይ የማይውል መሆኑን ባለማወቅ ዜጎች ለእንግልትና ለተጨማሪ ወጪ እየተዳረጉ ይገኛሉ።

በመሆኑም ሁሉም ሚስዮኖች የጉዳዩ አሳሳቢነት ከግምት በማስገባት ሚስዮኑ በሚገኝበት ወይንም በሚሸፍናቸው አገራት ትምህርት የሚከታተሉ ዜጎች በጉዳዩ ላይ ዕውቀት እንዲኖራቸው አመቺ በሆኑ መንገዶች እና ሚስዮኑ በሚጠቀማቸው የማህበራዊ ሚዲያ አማራጮች በሙሉ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ እንዲሰራ እናሳውቃለን።

ከሰላምታ ጋር

አምባሳደር ሲራጅ ረሺድ ጁንዲ
የቆንስላ ጉዳዮች ዳይሬክተር ጀኔራል

ግልባጭ ፡-

- ለዜጎች መብት ማስከበር ዳይሬክቶሬት
  የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር
  <u>አዲስ አበባ</u>

Filwuha, Addis Ababa,Ethiopia. P.O.Box 393
Call: +251 115 51 73 45 | Fax: +251 115 51 43 00
Email:- Info@mfa.gov.et
Web:- www.mfa.gov.et